**ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የቅንጅት ፕሬዚዳንት ሰኔ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በቅንጅት 1ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ መክፈቻ ላይ ያደረጉት ንግግር**

## የተወደዳችሁ የጉባኤ አባላት
## ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች
## ክቡራትና ክቡራን

ከሁሉ አስቀድሜ ይህን ታሪካዊ ጉባኤ ለማካሄድ እንድንችል እድሜና ጤናውን ላደለን ፈጣሪያችን ክብር ምስጋና ይድረሰው እላለሁ፡፡

የተለያዩ እንቅፋቶችን በፅኑ እምነታችሁ አሸንፋችሁ ለዚህ ጉባኤ ተካፋይነት የበቃችሁትን ሁሉ እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ፡፡

ለነፃነትና ዴሞክራሲ ሲካሄድ የቆየው ትግል ብዙ ችግሮችን ያየንበት ከሁሉም በላይ ብዙ ወጣቶች በአጠቃላይ ብዙኃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ መስዋዕትነት የከፈለባቸው ሲሆን እናንተ ደግሞ የዚህ መራራ ትግል ግንባር ቀደም ታጋዮችና አታጋዮች ስለሆናችሁ ታሪክ ተገቢውን ቦታ እንደሚሰጣችሁ አትጠራጠሩ፡፡ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ የሚካሄደው እንቅስቃሴ ዛሬም የሕዝብ ጥያቄ መሆኑ እናንተ ከሕዝቡ ጋር ተቀራርባችሁ ያላችሁት የምታውቁት ነው፡፡ ስለዚህ አሁንም ፓርቲያችሁ በእናንተ አዝማችነት የጀመረውን ትግል ይቀጥላል፡፡

ፓርቲያችን ከተመሠረተበት ከመስከረም 14/1998 ጀምሮ ያከናወናቸውንና የደረሰበትን ሁኔታዎች በአጭሩ አቀርባለሁ፡፡ ሁላችሁም እንደምታውቁት ከውህደቱ በፊት አራቱ ፓርቲዎች ሕልውናቸው ሳይነካ በጥምረት ምርጫውን ተሳትፈው ውጤቱ አመርቂ በመሆኑ ወደ ውህደት ከፍ እንዲል ከስምምነት ላይ ተደርሶ የውህደቱ ሰነድ ለምርጫ ቦርድ ቀረበ፡፡ ምዝገባውን ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ባለማጠናቀቁ ዛሬ ላጋጠመን የስም ሽሚያ ተዳርገናል፡፡ ይህ ጉዳይ ለክስ ቀርቦ ከተሰማ በኋላ ይኸው ለሐምሌ 16/2000 ዓ.ም ተቀጥሯል፡፡ የፓርቲያችን ስም እንደገና እንደሚመለስልን ተስፋ አለን፡፡ ሆነም ቀረም ምንም መሠናክል ከትግላችን እንደማያዘናጋን ሳረጋግጥ እናንተ የትግሉ አካል የሆናችሁትም እንደምትስማሙበት አልጠራጠርም፡፡

በወቅቱ ከምርጫው ጋር ተያይዘው የተከሰቱትን ችግሮች ለማርገብ ከመንግሥት ጋር ድርድር ተሞክሮ ነበር፡፡ ነገር ግን በመንግሥት ግትርነት ውጤታማ ሊሆን አልቻለም፡፡ ሁኔታውን ለሕዝብ አስረድተን በማያጠራጥር ሁኔታ የምርጫው ውጤት ተዛብቶ ፓርላማ መግባት ሕዝብን መጻረር ነው ብሎ የመረጠን ሕዝብ በመወሰኑ ፓርላማ ላለመግባት የፓርቲያችን ላዕላይ ምክር ቤት በአንድ ድምፅ ወሰነ፡፡

‹‹የሕዝብን ድምፅ አናስነጥቅም›› በማለታችን ወደ ወህኒ ቤት መወርወራችን ሁሉም የሚያውቀው በመሆኑ አሁን ዝርዝሩን መድገም አስፈላጊ አይመስለኝም፡፡ ያም ሆኖ ብዙዎቻችሁ በየአካባቢያችሁ ከሕዝቡ ጋር በመገናኘት ፓርቲያችን ከሕዝቡ ጋር መሆኑን በምሳሌነት ስለአስመሰከራችሁ ዛሬ እንደገና ለመገንባት ለምናደርገው እንቅስቃሴ ጥሩ መንደርደሪያ በመሆኑ ልትኮሩበት ይገባል፡፡

በሌላ በኩል እኛ በታሠርንበት አካባቢ ፀረ አንድነት ወገኖች በፓርቲው ላይ ያካሄዱት የመከፋፈል ደባ የሚያሳፍር እንደሆነ ሁላችሁም በኃዘንና በብስጭት ታዝባችኋል፡፡ ይኸንን በተመለከተ በአጭሩ ዛሬ ለማስረዳት የምሞክረው ሕዝብ እንዲገነዘበው እንጂ ሌሎችን ለመውቀስ እንዳልሆነ እንድታውቁልኝ እፈልጋለሁ፡፡

ከወህኒ ቤት እንደተፈታን የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍቅሩንና ያልተቆጠበ ድጋፉን በግልና በአደባባይ ስለገለፀልን በዚህ አጋጣሚ ከፍተኛ ምሥጋናችንን በእናንተ በኩል እንደምታደርሱልን አልጠራጠርም፡፡ በወቅቱም ሆነ ዛሬ በመገናኛ ብዙኃን መልዕክታችንን ማስተላለፍ ስላልታደልን ለወደፊት በያላችሁበት መጥተን ከሕዝብ ጋር ቀጥተኛ ውይይት እናካሂዳለን፡፡ በዚህ ጊዜ ለሕዝቡ ያለንን ፍቅርና አክብሮት በማያወላውል መንገድ እናስተላልፋለን፡፡

አሁን እንዳልኩት ሕዝቡ ከፍተኛ ፍቅር ሲያሳየን ጥቂት የተለየ አጀንዳ ያላቸው ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈሉ የሰማዕታትን ቤተሰቦች ማፅናናት ሲገባቸውና የሚሊኒየሙን በዓል ከአፈቀረን ሕዝብ ጋር መዋል ሲገባቸው በጥቂቶች ውሳኔ ወደ ባህር ማዶ ሄደዋል፡፡ ይኸንንም የብዙኃን ውሳኔ እያሉ ሲመጻደቁበት ታዝበናል፡፡ ሁላችሁም እንደምታውቁት ፓርቲያችን ልዩ ልዩ የውሳኔ ደረጃዎች አሉት፡፡ ከፍተኛው ይኸ ዛሬ የተሰበሰበው ጠቅላላ ጉባዔ ሲሆን ከዚያ ቀጥሎ 60 አባላት ያሉት ላዕላይ ምክር ቤትና ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ናቸው፡፡ ከላዕላይ ምክር ቤት 17 አባላት ተሰባስበው ውሳኔ ሰጥተናል አሉ፡፡ እኔም በወቅቱ ከፍተኛ ሕመም ላይ በመሆኔ በስብሰባቸው ለመገኘት አልቻልኩም፡፡ እንደምታውቁት በፓርቲያችን ሕገ ደንብ መሰረት የላዕላይ ምክር ቤት ስብሰባ ሊካሄድ የሚችለው ኮረም ሲሞላ ብቻ ነው ማለትም ከስድሳዎቹ 31 አባሎች ሲገኙ ብቻ ነው፡፡ ታዲያ አፍራሾች በጥቂት የተመራረጡ ግለሰቦች የተካሄደውን ውሳኔ የብዙኃን ውሳኔ ያሉት የሚያውቀውን አባልም ለማሳሳት የተካሄደ መሆኑ በግልፅ ታይቷል፡፡ ይባስ ብለው በግል የተመካከሩበት ተቃውሞ እንዳይገጥመው ሲባል ሌሎች የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ባለመታሠራቸው ብቻ ባካሄዱት ውይይት እንዳይሳተፉ አገዱ፡፡ ይኸንን ሂደት ተቃውሞ በቃልም ሆነ በጽሑፍ ብገልፅም የሕዝብን ሳይሆን የቡድን አጀንዳቸውን ለማሟላት ብቻ በእምቢተኝነት ተቻኩለው ሄደዋል፡፡ ከሁሉም በላይ ዛሬም የሚያሳዝነው ብዙ ወጣት ታጋዮች ሳይፈቱ ጉዳያችን ፋይዳ ማሳጣታቸው ነው፡፡ የነዚህን እስረኞች ዛሬ አንስተን ለማስፈተት እየጣርን እንገኛለን፡፡

ሌላው አንኳር ጉዳይ እነዚሁ ጥቂት ግለሰቦች እስር ላይ በነበርንበት ጊዜ በውጭ አገር የሚገኙትን የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች በወኪሎቻቸው አማካኝነት ሲከፋፈሉ በመቆየታቸው ፓርቲያችን ይኸንን ችግር መፍታት ትኩረት ከሰጣቸው ሥራዎች አንዱ እንደነበር የማይካድ ነው፡፡ ይኸም ግራ ቀኙን መርምሮ ማግባባት የሚያስፈልገው መሆኑ እየታወቀ እነዚሁ በቡድን ዝግጅት ያደረጉት ብቻቸውን ሄደው አንዱን ብቻ በመደገፋቸው ያሉበት ጠንካራ ደረጃ ለማድረስ ብዙ ዓመታት የተለፉባቸውን ድርጅቶች በትነዋል፡፡ ይህ አፍራሽ ሚናቸው ወደ ኢትዮጵያም ቢዛመት የሚያመጣው መዘዝ ከፍተኛ በመሆኑ ይኸንን አፍራሽ ሚና በተጫወቱ ግለሰቦች ላይ ጊዜያዊ እግድ አድርጌያለሁ፡፡ ይህ ጉዳይ ቅፅበታዊ ውሳኔ ባይሰጥ ዛሬ ፓርቲያችን የበለጠ ተበታትኖ የሕዝብ ትግል ውጤት መና ይቀር ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ ላዕላይ ምክር ቤቱ ውሳኔ እንዲሰጥበት መረጃው ቀርቧል፡፡

ይህ ቡድን በከፊል ወደ አገር ተመልሶ መከፋፈሉን እንዳይቀጥል አምስት ግለሰቦች በጊዜያዊነት መታገዳቸውን ከዚህ በላይ አስረድቻለሁ፡፡ ነገር ግን ሌሎቹ ግብረ አበር መሆናቸውን ባውቅም ይታረማሉ በሚል ያላንዳች ገደብ በላዕላይ ምክር ቤት አባልነት እንዲቀጥሉ ፈቅጃለሁ፡፡ ነገር ግን ሌሎቹ ከታገዱት አምስቱ ጋር በማበር ሁለት ፓርቲዎች አቋቁመዋል፡፡ ሌላ ፓርቲ ማቋቋም መብታቸው ቢሆንም በቅንጅት ላይ ግን ምንም ዓይነት ደባ እንዲቀጥሉ አንፈቅድም፡፡ እኛ የነሱ አፈንግጦ መሄድ ቢያሳዝነንም ሌላ ፓርቲ ማቋቋም መብታቸው ስለሆነ ከእንግዲህ ምንም ዓይነት ተቃውሞ አይኖረንም፡፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲቆሙና ለዴሞክራሲ እንዲታገሉ አደራችን የጠበቀ ነው፡፡

በየወቅቱ በሚከሰቱ ችግሮች ፓርቲያችን መከላከል ቢኖርበትም በምንም መልኩ የሕዝብ ወገናዊነቱንና ለዴሞክራሲ አጠንክሮ ወደፊት መገስገሱን የሚገታው አይኖርም፡፡ ስለዚህ በውጭ አገር በነበርኩበት ወቅት የፈራረሱትን የድጋፍ ድርጅቶች እንደገና አቋቁመን አዲስ አመራር መርጠው ሥራቸውን በማጣደፍ ላይ ይገኛሉ፡፡

ከዚህም በላይ ፓርቲያችን በአገር ወዳድ ምሁራን እውቀት ለመጠቀም እንዲችል አንድ አማካሪ ቡድን አቋቁሞ ሥራ ጀምሯል፡፡ ይህም የተገነባው በልዩ ልዩ መስኮች ከፍተኛ እውቀት ባላቸው ኢትዮጵያውያን ስለሆነ ለድርጅታችን ዘመናዊነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከማድረጋቸውም በላይ ለወደፊትም ለኢትዮጵያ ልማት የማይናቅ ኃይል እንደሚሆኑ እምነታችን ከፍተኛ ነው፡፡ ይህ አማካሪ ቦርድ የተገነባው በሳይንስ፣ በጤና፣ በትምህርት፣ በፖለቲካ፣ በእርሻ እንዲሁም በሌሎች አገር ግንባታ መስኮች የላቀ ደረጃ የደረሱ የአገር ልጆች ስለሆነ ተስፋ የጣልንበት ነውና በየወቅቱ ለፓርቲያችን ሥራ አስፈላጊውን አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚል ተስፋ አለን፡፡

ከተፈታን በኋላ በአገር ውስጥም ብዙ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ብዙ ታጋዮች የሚደርስባቸውን ችግር ባለመፍራት በየአካባቢው ድርጅታችንን እንደገና በእግሩ ለማቆም ከእናንተ ከሕዝቡ መሐል ከመጣችሁት ጋር በመተባበር ከፍተኛ ሥራ መሥራቱን ተረድቻለሁ፡፡ ለዚህም የወቅቱን አመራር አባላት በእናንተ ፊት

እንዳመሰግናቸው ይፈቀድልኝ፡፡ ይህንንም የምለው ሥራው በአግባቡ በመጀመሩ እንጂ በመፈጸሙ እንዳልሆነ እንድታውቁልኝ እወዳለሁ፡፡

## ክቡራትና ክቡራን

የሰው ልጅ የዚህ ዓለም ሕይወቱ በተለያዩ የትግል ሂደቶች የሚፈተን ነው፤ ጠባቡን የዕለት ኑሮውን ለማሸነፍ ከሚያደርገው ትግል ጀምሮ እስከ ግል መብቱን ማስከበር ድረስ ከዚያም አልፎ የሕዝብን መብት እስከማስከበር ድረስ በሰው ልጅ ሕይወት ላይ እየተፈራረቁ የሚፈትኑትን የዚህ ዓለም ኑሮ ውጣ ውረዶች ለአንድ አፍታ በአእምሮአችን ስናስባቸው እጅግ ብዙና ውስብስብ ናቸው፡፡ የዚህ ዓለም ኑሮ ፈታኝ በመሆኑም ቢያንስ ፈተናውን ለማቅለልና የተሻለ ሕይወት ለማግኘት ሲል የሰው ልጅ በሁሉም የሕይወቱ አቅጣጫ በፅኑ ይታገላል፡፡ ተፈጥሮን ይታገላል፤ ሰው ሰራሽ ችግሮችን ይታገላል፤ ከዚያም አልፎ ያሉትን ውጥንቅጥ አስተሳሰቦች ይታገላል፡፡ በዚህ ትግሉ አካባቢውን የተሻለ የሰው ልጅ መኖሪያ ብቻ ሳይሆን መደሰቺያ ሊያደርግ ይሞክራል፡፡ ይህ በአገር ደረጃ በሁሉም የዓለም ሕዝብ ዘንድ የሚታይ የሰው ልጅ ውጣ ውረድ አንዱ ፈርጅ ነው፡፡ ትግላቸው የተሳካላቸውና የአካባቢያቸውን ፀጋ በቁጥጥራቸው ሥር ያደረጉ አገሮች የሕዝባቸውን ፍላጐት በመጠኑም ቢሆን እያረኩ ነው፤ መልካም አስተደደር መስርተውም የአገራቸውን ፀጋ ለሕዝባቸው ጥቅም እያዋሉ ይገኛሉ፡፡ በዚህም የሕዝባቸው ቀፈን የሆነውን ረሀብን ከአገራቸው አስወግደዋል፡፡ የኛም የትግል ትኩረት መልካም አስተዳደር በአገራችን ተመስርቶ ብሔረሰብ ከብሔረሰብ ተከባብሮና ተፈቃቅሮ በተረጋጋ ሠላምና በጋለ የሥራ መንፈስ አገራችንን የምንገነባበት ሁኔታ እንዲመቻችልን ለማድረግ ብቻ ነው፡፡

ዛሬ አገራችን በሁሉም ነገር ኋላ ቀር ሆናለች፡፡ በዓለም ላይ የመጨረሻ ደሀ ከሚባሉት ምድቦች የመጨረሻዋ ደሀ አገር ተብላ በረሀብተኛነትም ተፈርጃለች፡፡ ይህ ሁሉንም ዜጋ የሚያስቆጭ መሆኑን ከጥያቄ ውስጥ አይገባም፡፡ ስለዚህም ሁላችንም፣ የድህነታችንን መንስኤ ምን እንደሆነ መጠየቃችን አይቀርም፤ ጠንካራ ሕዝብና ለልማት የተመቻቸ አገር አለን እያልን የዚህ ጥንካሬ ተቋዳሽ አልሆንም፡፡ ለምን ይሆን? ብዙ ሰው ብዙ ሰበብ ሊፈጥር ይችላል ነገር ግን መልሱ ግልፅ ነው፡፡ ያለውን የሰውም ሆነ ቁሳዊ ሃብት ለሕዝብ ጥቅም እንዲውል የሥራ ፍላጎትን ማነሳሳት የሚቻለው ሕዝቡና አመራሩ ሲተማመኑ ነው፡፡ ይህ ደግሞ እንዲሁ በመፈለጉ የሚመጣ ሳይሆን ሕዝብን የሚያከብር በሕዝብ የተመረጠ አመራር ሲኖር ብቻ ነው፡፡

ይህን ሕዝባዊ የመንግሥት ሥርዓት ለማምጣት በዲሲፕሊን የሚመራ ያልተቋረጠ ሰላማዊ ትግል ማካሄድን ይጠይቃል፡፡ እናንተም የተሰባሰባችሁት የዚህን ዓይነት ጠንካራ ፓርቲ ለመገንባት ነው፡፡ አንዳንዶቹ በአንድ ጥሪት የተፈለገው ባለመገኘቱ ተስፋ ቆርጠዋል፡፡ ለዴሞክራሲ የሚካሄደው ትግል እልህ አስጨራሽ

መሆኑን አውቀን የገባንበት በመሆኑ አሁን ወደ ጥርጣሬ የምናዘነብልበት ጊዜ አይደለም፡፡

የደረሱትን ምስቅልቅሎች ሕዝብ በብዙ መልኩ እንደሚተነተነው አንጠራጠርም፡፡ ብዙ መስዋዕትነት የተከፈለበት ፓርቲ በመሆኑም በአመራሩ መከፋፈልም ከፍተኛ ቅሬታም ቢሰማው እኛን ተስፋ የሚያስቆርጠን ሊሆን አይገባም፡፡ እውነትን ይዘን ከተጓዝን ሕዝብ የራሱን ውሳኔ አድርጎ አብሮን እንደገና እንደሚታገል ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ የለንም፡፡ የሕዝብ ወገን ስለሆንን በሚደርሱብን ችግሮች አንበረግግም፡፡ የምርጫውን ውጤት ተነጥቀንም የዴሞክራሲ ትግላችንን እንደገና ተያይዘናል፡፡ የዓለምን ያለፉትንም ሆነ የዛሬ ክስተቶች ስንቃኝ በአንድ ወቅት በተገኘ ውጤት ብቻ የረጅም ጊዜ የዴሞክራሲ ግንባታ እንደማይረጋገጥ ሁሉ በአንድ ወቅት ሽንፈት ብቻም ሂደቱ አይገታም፡፡ በዚህም መሠረት ሰላማዊ ትግላችን ስልታዊ በሆነ መንገድ መቀጠል እንዳለበት እናምናለን፤ ውጤታማ ለመሆንም ገና ከፍተኛ መስዋዕትነት መክፈል እንዳለብን እንገነዘባለን፡፡ ይህ ደግሞ ሊያጠናክረን ይገባል እንጂ የሚያዳክመን ሊሆን አይችልም፡፡

የፓርቲያችንን ግንባታ ያላንዳች ማወላወል ለማፋጠን ያለፈውን ሂደት ገምግመን ከዚያም አስፈላጊውን ትምህርት ቀስመን ለወደፊት ከባድ ትግል የምንሰለፈው ዛሬ ነው! ውስጣችንን መርምረን ድክመታችንን አስወግደን ለሌላ ሰላማዊ የሕዝብ ድል የምንዘምረው ዛሬ ነው! እያንዳንዳችን ጥርጣሬን አስወግደን የውስጥ ጥንካሬያችንን በሥራ ላይ ለማዋል ቆርጠን የምንነሳው ዛሬ ነው! ለሕዝብ ተአማኒነታችንና ለእውነት መቆማችንንም የምናረጋግጠው ዛሬ ነው!

ፓርቲያችን ዛሬም አንድ ነውና ተረጋግታችሁ በትግሉ መስክ ተሰማሩ አሁንም ደግሞ ቅንጅት አንድ ነው ስል እውነታውን ያንፀባረቀ ነው እንጂ ምኞታዊ እንዳልሆነ አረጋግጣለሁ፡፡

ቅንጅት አንድ ነው!
ኢትዮጵያም አንድ ናት!
እውነተኛ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ይሰፍናል፡፡